# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)


ሚያዚያ 20 ቀን 2000 ዓም

## ከሀዲው ወያኔ ሀገራችንን ለባዕድ ሲሸጥ መቃወም ግዴታችን ነው

የመለስ ዜናዊ ከሀዲ አገዛዝ የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን አሳልፎ በመስጠቱ የሱዳን ወታደሮች ድንበር አልፈው የሀገራችንን መሬት በመያዝ በነፍሶ ገበያ ተራራ አካባቢ(ቋራ) ኢትዮጵያዊ አርሶ አደሮችን ገድለው፣ ቤታቸውን አቃጥለውና ይባስ ብለውም ከ30 በላይ ዜጎችን አስረው ወደ ሱዳን ወስደዋል፡፡ ይህ ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ውርደትና ቅሌት መሆኑን ስንገነዘብ ይህ የወያኔ አገዛዝ ምንኛ ፀረ ኢትዮጵያ መሆኑን መረዳት መገደዳችን አልቀረም፡፡

የወያኔ አገዛዝ ሥልጣን ከጨበጠ ጀምሮ ኢትዮጵያን ለመገነጣጠልና ለማዋረድ ባለው አቅሙ ሁሉ ሲጥር መቆየቱ የታወቀ ነው፡፡ ከጎንደርና ከወሎ ለም መሬቶችን ወደ ራሱ (ክልል አንድ) ከመውሰዱ ሌላ ለባዕድ ሀገር ማለትም ለሱዳን የጎንደርን መሬት አሳልፎ መስጠቱ ደግሞ ዛሬ ግልፅ ሆኗል፡፡ ከቋራ ጎንደር እስከ ወለጋ ያለውን የኢትዮጵያ መሬት ለሱዳን የሰጠው ይህ ከሀዲ የወያኔ ቡድን አሳፋሪ ድርጊቱን ለመሸፋፈን ቢጥርም ወንጀሉ የማይደበቅ ሆኗል፡፡ የሱዳን አርሶ አደሮች መሬቱን በኪራይ ደረጃ እየሰሩበት÷ ከግብርናው ለኢትዮጵያ ትርፍን ይሱጣሉ ብሎ አዲሱ ለገሰ የዋሸው በዚህ ደረጃ የሚጠቀስ ነው፡፡ ግንጠላን የደገፈው ወያኔ ዛሬ ደግሞ የሀገሪቱን መሬት ቆርሶ ለሱዳን መስጠቱ የሚያስገርም ሊሆን አይችልም፡፡ በቋራ ገፅታ ድንበራችን ነፍሶ ገበያ ሳይሆን በሺንፋ ወንዝ መሆኑን ከዓመታት በፊት ኢሕአፓ ያስከበረው ሆኖ ሳለ ዛሬ ወያኔ ይህንን ሰርዞና ሽሮ ለም መሬትን ለሱዳን መስጠቱ ክህደት እንጂ ሌላ ምንም ሊሆን እንደማይችል ግልፅ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷን አስጠባቂ መንግሥት የላትምና መሬቷ በከሀዲ ኃይል ለባዕድ መሰጠቱ የሚያሰገርም ባይሆንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን ዓይን አውጣ ክህደት በመቃወም መነሳትና መታገል እንዳለበት ደግሞ አከራካሪ አይደለም፡፡

በአሁኑ ወቅት የጎንደር ሕዘብ ይህን ክህደት ለመቃወም ተነስቶ ይገኛል፡፡ ጉዳዩ ብሔራዊ ነውና፣ ሁሉን ኢትዮጵያዊ የሚመለከት ነውና የሀገራችን መሬት ለሱዳን ተሰጥቶ ሱዳንም ዜጎችን ሲገድልና ሲያስር በዝምታ ማየት የሚቻል አይደለም፡፡ እምቢኝ ብሎ ትግል ከጀመረው የጎንደር ሕዝብ ጎን ሁሉም ኢትዮጵያዊ በመቆም ይህን የወያኔ ክህደት ሊቃወምና ሊታገል ይገባል፡፡ ሀገር ተቆርሳ ለባዕድ ስትሰጥ በዝምታ ማየቱ ለዜጎች ወንጀል ነው፡፡ ስንት ደም ፈሶና መስዋዕትነት ተከፍሎ የተከበረውን ሀገራዊ ግዛት/መሬት ፀረ ኢትዮጵያ የሆነ ቡድን ሊሸጥና ለባዕድ ሊያስረክብ ሲነሳ በአስቸኳይ መቃወምና መታገሉ ግዴታ ነው፡፡ የሱዳንን የመስፋፋት ጥረት በተመለከተ ኢሕአፓ በቆራጥነት ታግሎ የገታው መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ፀረ ኢትዮጵያ የሆነው የወያኔ አገዛዝ ግን የኢትዮጵያን በደምና በመስዋዕትነት የተከበረ መሬት ለሱዳን አሳልፎ መስጠቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ ቁጣና ተቃውሞ የሚያስነሳ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ይህ ፀረ ሕዘብ አገዛዝ ካልተወገደ ሀገራችን ኢትዮጵያ ጥቃት በጥቃት የሚደራረብባት መሆኗ አይቀሬ ነውና ሁሉም ኢትዮጵያዊ ይህን ፀረ ኢትዮጵያ የወያኔ አገዛዝ ለማደባየትና ለማስወገድ በጋራ እንዲነሳ ኢሕአፓ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡


EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France